# ለማ እና ገዱን ጥፋተኛ ያደረገው የኢህአዴግ መግለጫ ሲፈተሽ

[በወንድወሰን ተክሉ-ጋዜጠኛ]

**መነሻ-ጭብጥ ነጥቦች-

** 1ኛ-ለሁለት ጎራ መከፈሉ የተነገረለት የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ዝግ ስብሰባ ከ17ቀናት  ንትርክ በሃላ በስምምነት አንድ ሆነን ስብሰባውን አጠናቀናል ሲል ቅዳሜ መግለጫ አውጥቷል።

** 2ኛ-በመግለጫው ላይ ለህወሃትና ብሎም ለኢህአዴግ ድርጅታዊ መሰነጠቅ ምክንያት የሆነውን ህዝባዊ ዓመጽ መንስኤን የድርጅቱ የስራ አስፈጻሚው አመራር አካል ስህተት ውጤት ብሎ የደመደመ ሲሆን በተጋዳኝነትም በህገሪቷ ውድጥ በተፈጠረው ከፍተኛ እድገት ምክንያት የፍላጎት ማደግ የወለደው ጥያቄ ነው ሲል ተሳልቋል።

**3ኛ-ድርጅቱ በመግለጫው ውስጥ መረን ያጣው ዘረፋ፣የአስኳሉ ህወሃት የበላይነትና አምባገነንነት፣ያልተመጣጠነ የሀብትና ስራ ክፍፍል እና ብሎም ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች እንደ ችግርም ተደርገው ያልተጠቀሱና ተውጠው የታለፉ ግን በሀገሪቷ ውስጥ ለተፈጠረው ህዝባዊ ዓመጽ ዋና መንስኤ እንደሆነ መቀበል አልፈለገም።

**4ኛ-ህወሃት ውስጠ ድርጅቱን እና ኢህአዴግን የሰነጠቀውን መንስኤ በአግባቡ ሳያነሳና ለመመለስም ምንም ሳይጥር ልክ እንደ ተሰበረ ነፍስ አልባ እቃ ስንጥቁን ብቻ በመጠገን ድርጅታዊ መሰነጣጠቅን አድሼና ጠግኜ አስተካክዬዋለሁ በማለት ለህዝብ መመለስ የሚገባውን ወሳኝ ነጥቦች ዘሎት ታይታል።

**5ኛ-እነ አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና አቶ ለማ መገርሳ ከእነ ቡድናቸው በጥፋተኝነታቸው መልቀቅ አለባቸው በሚል ውሳኔ ከስልጣን መሰናበቻ መንገድ የቀየሰላቸው ሲሆን የመሰረቱት የሁለቱ ክልሎች ትብብር፣አንድነትና አጋርነት ከማበረታታት ይልቅ ለኢህአዴግ ህልውና ጠንቅ ስለሆነ ህገ-ወጥ ነው በማለት እንዲቆም የተወሰነበት መሆኑን የተረዳሁበትን መግለጫ እንደሚከተለው ፍተሻውን አቀርባለሁ።

*******

**የህወሃት የበላይነትን የማስቀጠልን አግባብነት ያሰመረው መግለጫ መከላከያውን ለወሳዳቸው እርምጃዎች አመስግናል-

ብዙዎች፣የህወሃትን ፖለቲካ በቅርበት ላላወቁ 17ቀን ከፈጀው የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ይገኛል ብለው የጠበቁት ሳይሆን ያልጠበቁትን ውጤት ድርጅቱ ስብሰባውን በጨረሰ ማግስት ዛሬ በመግለጫው ይፋ አድርጋል።

ወደ ስምንት ገጽ ከተጠጋው የድርጅቱ መግለጫ ላይ ምን አዲስ የሆነ ነገር ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይዞ ቀርባል ቢባል ፈጣኑ እና አጭሩ መልስ ምንም የሚል ይሆንና በዚያው የመልስ ፍጥነት በእርግጥ ድርጅቱ በህዝቡ ላይ የባሱ አስከፊ የሙብት ረገጣዎችን እንደሚወስድ ገልጻል በማለት እንደ አዲስነቱ ልንጠቅሰው እንችላለን።

ህወሃትን የማያውቁ እጅግ ብዙ ጠበቁ- በተለይም አዲሱን የህወሃት አመራርን ጠንቅቆ ያላወቀ ብዙ አዲስ ነገር ቢጠብቅ -አያስደንቅ በማለት የተሰብሳቢዎቹን ፍሬከርሲኪ እንቶፈንቶን በመጨረሻ ላይ እንደተነገረን መረዳት ችለናል።

በእውኑ ነብር ዥንጉርጉርነቱን-ኢትዮጵያዊም ኢትዮጵያዊነቱን መለወጥ ይቻለዋልን? እንዳለው መጽሃፍ ቅዱስ እኛም በእርግጥ ከህወሃት አንዳች አዲስ ነገር ይገኛልን ?ስንል ደጋግመን ለሕዝባችን ገልጸናል-ለሚሰማም ተናግረናል።

የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ አመራር አካል ከ17ቀናት ዝግ ንትርክ በሃላ ዛሬ ባወጣው ባለ 8ነጥብ የአቋም መግለጫ ላይ ወሳኝ የሆኑ ሶስት ውሳኔዎችን ለአብነት ልጠቅስ እወዳለሁ-

1ኛ-በሀገሪቱ ውስጥ ለተፈጠረው ሀገር አቀፍ ግጭትና ችግሮች ዋና መንስኤው የድርጅቱ አመራር ጉድለት በተለይም የስራ አስፈጻሚው አመራር አካል ጥፋት  መሆኑን ከስምምነት ላይ መደረሱን የገለጸበትን።

2ኛ-በሁለት ቡድኖች መካከል የኢህአዴግን ህልውና ለአደጋ የሚዳርግ አንድነትና ትብብር አደገኛ መሆኑን አውቆ ድርጅቱ ድርጊቱን ለማስቆምና ዳግምም እንዳይፈጠር ለመከላከል መወሰኑን የገለጸበትን ውሳኔና

3ኛው-እነዚህ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተከሰተው ህዝባዊ ዓመጽ መንስኤ የሆኑት የአራቱ ድርጅት አባላት በአስቸካይ ውስጠ ድርጅታዊ ግምገማና ለውጥ እንዲያካሂዱ ወስነናል በማለት ያስተላለፋቸውን ሶስት ነጥቦች እድምታና ተፈጻሚነታቸው ላይ ማሳወቅ ያለብኝን እውነታ ለማካፈል እወዳለሁ።

ከእነዚህ ሶስት ወሳኝ ካልካቸው ነጥቦች በተጓዳኝ ድርጅቱ ላለፉት ሩብ ምእተ ዓመታት ከተጋዘበት [ማለትም በህወሃት የበላይነት ስር ማለቱ ነው]መንገድ ለማስወጣት የሚያስቡትን በጽኑ ይታገላል-ሌላ አዲስ አካሄድም ለመጀመር አያስፈልገውም በማለት ለድርጅታዊ ተሃድሶ በሩን እንደማይከፍት ለኢትዮጵያዊያን በይፋ የገለጸበትና ከሁሉም በላይ ለመከላከያ ሰራዊቱና ለጽጥታ ሃይሎች የሰጠው ሞቃ ያለው የምስጋና ቃል ሀገራችን ለአዲስ ዙር ደም አፋሳሽ ፍልሚያ ወገባን አደግድጋ ማሰር እንዳለባት ያዘዘ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በመቶዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሃን ላለቁበት ጭፍጨፋ ትንፍሽ ያላለው መግለጫ ከአሁን በሃላ በግለሰብም ሆነ በቡድን መንገድ በመዝጋትና ለተቃውሞ በመውጣት የሚያስቸግሩ ወጣቶችን እርምጃ በሃይል እንደሚያስቆምና እርምጃ እንደሚወስድ ዝቷል-ውሳኔውንም ይፋ አድርጋል።

የእኛ ነገር- በተለይም የህወሃት/ኢህአዴግ ነገር ትሻልን አገባሁ ብዬ ትብስን አመጣሁ እንዳለው መከረኛ ባልተቤት አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዢው ፓርቲ በሀገሪቱ ውስጥ እየተካሄዳ ያለውን ሁኔታ በመረዳት አረጋጊና መብት አስከባሪ ማሻሻያዎችን ያሳልፋል ብለው ሲጠብቁ ድርጅቱ ግን ጨፍጫፊውን ሰራዊት በማመስገን፣መብቱን ጠያቂውን ክፍል በመኮንና የህዝባዊው ዓመጽ ዋና አስኳል የሆነውን የህወሃትን የበላይነት በኢህአዴግ ውስጥ በማጽናት "ምን ታመጣላችሁ-እስቲ ሞክሩኛና ይለይልን" የሚል እብሪተኛው ፈርኦን ሆናል።

** በአቶ ለማ መገርሳና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተላልፋል-ቀጣዩም እነሱን እና ቡድናቸውን ማጥፋትና ማክሰም ይሆናል-

ከቀናት በፊት በከተብኩት መጣጥፌ ህወሃት የብአዴኑን አቶ ገዱ አንዳርጋቸውን እና የኦህዴዱን አቶ ለማ መገርሳን ከእነ ቡድናቸው ለማጥፋት ወስናል በማለት ገልጪ ነበር። በእለቱ ሁለቱን ቡድኖች ለማጥፋት ህወሃት የራሱን ተመክሮ በመጠቀም በሀገሪቷ ውስጥ ለተፈጠረው ፖለቲካዊ ቀውስ የህወሃት የበላይነትና አምባገነንነት የፈጠረው ሳይሆን የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚው አመራር ጥፋት ነው በሚል ማሳመኛ ነጥብ በሃይልም ሆነ በብልሃት በማሳመን ነው ስል ገልጬ ነበር።

በዛሬው የድርጅቱ መግለጫ ላይ ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው የድርጅቱ አመራር በተለይም ይላል የስራ አስፈጻሚው ክፍል ጥፋትና ጉድለት መሆኑን ስምምነት ላይ ተደርሳል ሲል ከህወሃት በስተቀር ጠ/ሚ ሃይለማርያምን ጨምሮ እነ አቶ ገዱን እና አቶ ለማን ጥፋተኛ ያደረጋል።

በተለይም ውሳኔው በሁለቱ ክልል መሪዎች ላይ ያነጣጠረ መሆኑን የሚያሳየው በመግለጫው ውስጥ "በተለይም በክልሎችና በተጎራባቾ ጎሳዎች መካከል እጅግ ከፍተኛ የሆነ ግጭት ሊፈጠር የቻለው የክልሎቹ አመራሮች በተጎናጸፉት ህግ-መንግስታዊ ስልጣን በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ጥፋት እንደሆነ ከመስማማት ደረጃ ተደርሳል" የሚለው አባባል ሲሆን ይህም አቶ ለማ መገርሳና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው በክልላቸው ውስጥ የተከሰተውን ብሄር ተኮር ግጭት ማስቆምና መቆጣጠር ሲችሉ ሆን ብለው አይተዋል በማለት ሲወነጅላቸው ይታያል።

ድርጅቱ በሁለቱ ክልሎች መካከል እየተካሄደ ያለውን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና የጋሪዮሽ ትብብርን ስራ እንደ የሀገር ጥቅም ይልቅ እንደ የኢህአዴግ ህልውና አደጋ በመቁጠር ያወገዘው ሲሆን ለማስቆምም መወሰኑን ገልጻል።

እንግዲህ ታድሼና ተለውጬ መጥቻለሁ እያለ ያለው የዶ/ር ደብረጺዮን መራሹ ህወሃት ነው የህዝቦችን ህብረትና አንድነትን እንደ የህልውናቸው አደጋ በመቁጠር መቆምና መፍረስ አለበት የሚል አስደማሚ ውሳኔን ሲያስተላልፍ የምናየው።

ድርጅቱ ካስተላለፋቸው ባለ8ነጥብ ውሳኔዎች ውስጥ ከላይ ያሰፈርኳቸው ሶስት ነጥቦች ሙሉ በሙሉ በጸረ -አቶ ለማ መገርሳና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ቡድን ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ ለመረዳት ምንም የውስጥ ምንጭና መረጃ ምስክር የሚያስፈልግ አይደለም።

ህወሃት የበላይነቱን ያስጠበቀበትን ውሳኔ በዚህ መልኩ ካሳለፈ በሃላ ለይስሙላም ቢሆን የፖለቲካው ምህዳር በመጥበቡና የጥምር ፖርቲ ፖሊሲ በመደፍጠጡ የተፈጠረውን የአንድ ሃሳብ ገዢነትን እንደችግር ጠቅሶ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በነጻነት የሚሳተፉበትን እና የነጻ ፕሬስ ህትመቶች ለህዝብ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ድርጅቱ ለመስራት ወስናል ሲልም አትታል።

ለተፈጠሩት ሀገራዊ ትርምሶች የስራ አስፈጻሚው አመራር አካል ጥፋት በመሆኑ ድርጅቱ በከፍተኛ መጸጸትና ሀዘን ጥፋተኝነቱን እየገለጸ ህዝቡን ይቅርታ ይጠይቃል "ሲሉ እነዚህ በጥፋተኝነት የተፈረጁ አመራሮች ዛሬ ካሉበት ወሳኝ ቦታና ስፍራ አንጻር ሽሮ መሾም ባይችልም በይደር ግን አመራሮቹን የመሞገቻ ሞራልና ህጋዊነትን ከወዲሁ በመንሳት ለቀጣዩ ሹም ሽር እንዳመቻቻቸው መረዳት ይቻላል።

የአቶ ለማ መገርሳ እና አቻቸው አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ቀጣይ እጣፈንታ ከስልጣን መወገድ አሊያም የጀመሩትን የህዝብን ጥያቄ የማስተጋባት አቋም አጠንክረው በመቀጠልና ከህዝባቸው ጋር በመሆን የተፍረከረከውን ስርዓት ለቀብር ማብቃት አሊያም በፍርሃት ታጅለው ህዝቡን እያስገደሉና እያስጨፈጨፉ በቀጣይ የህወሃት ሰለባ መሆን ብቻ ይጠብቃቸዋል።

ሁለቱ የክልል መሪዎች በየትኛው ጎራ እንደሚገኙ ወሳኞቹ እነሱ እንጂ እኔ ባልሆንም ዛሬ በድምጽ ብልጫ የተሸነፉበትንና የማያምኑበትን አቋም ይተገብራሉ ብዬ ግን በሙሉ ልቤ ለማመን ይከብደኛል።

ላለፉት ሁለት ተኩል ዓመታት ለፍትህ፣ለእኩልነት፣ለህግ የበላይነትና ለሰብዓዊ መብት መከበር እየታገለ ያለው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም የሁለቱ ክልሎች ህዝብ ከኢህአዴግ የስራ አስፈጻሚ አመራር ስብሰባ መግለጫ ውስጥ የተወሰነበት እንጂ የተወሰነለት አንዳችም ነገር የሌለው ሲሆን ሁኔታው የጀመረውን ትግል በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥልና ብሎም ትግሉን ለነጻነቱ እንዲያፋፍም የሚያስገድደው እንደሆነ ግን መረዳት አያዳግትም።

በቅርቡ በጨለቆ 18አርሶ አደሮችን በግፍ የጨፈጨፈው ሰራዊት ከተጨፍጫፊዎቹ ውስጥ 5ቱ የአንድ ቤተሰብ አባላት ሰለባ የሆኑበት ትዝታ እጅግ ትኩስ በሆነበት ወቅት ስለሰላባዎቹ ፍትህ ማግኘት ያልተነፈሰና ሀዘኑን እንካን ያልገለጸው መግለጫ ጨፍጫፊውን የመከላከያና የጸጥታ ሃይሉን ማመስገን የሚያስተላልፈው መልእክት በቀጣይ የምንሰማቸው ጭፍጨፋዎችን እንጂ ፍትህን እና ተጠያቂነትን ስላልሆነ የትግሉ ግለት እንደሚጨምር ይታየኛል።

ከብዙ የሀሳብ መለያየትና መከፋፈል በሃላ በመጨረሻም ለመስማማት በቅተናል የሚለውን ቃል -በቃል ወስዶ ኢህአዴግ ያልተከፋፈለና አንድ የሆነ ነው የሚል የዋህ ቢኖርም እውነታው ግን ድርጅቱ በአሁኑ ሰዓት በማይጠገን እና በማያገግም ሁኔታ ለሁለት የተሰነጠቀ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

የህወሃትን የበላይነት ለማስጠበቅ ሲባል በተወሰደው እርምጃ ለሁለት የተሰነጠቀው ኢህአዴግ ስንጥቁን እና ውስጣዊ ብስባሴውን በጠነከረ ዲሲፕሊን ለመጠገን እየጣረ "አንድ ለመሆን ተስማምተናል" እያለ በሚጥርበት ወቅት ኢትዮጵያዊያን ደግሞ ወደ ስብሰባው አዳራሽ ልከውት የነበረውን የተወሰነ ሀሳባቸውን አሰባስበው በአንድ ሀሳብ ስርዓቱን መታገል ተያይዘዋል።

የዓመጽ ሁሉ መንስኤ ጭቆና ነው። የጭቆና ምንጬ ደግሞ ጨቋኝ ሃይል በአንድ ሀገር ስልጣነ ወንበር ላይ ተፈናጦ የግል[ቡድናዊ፣ ድርጅታዊ] ጥቁሙን ብቻ በማስጠበቅ የሚያካሄደው አገዛዝ ሲሆን ይህን መሰሉ ስርዓት ከተቆናጠጠበት ህዝባዊ ስልጣን እስኪለቅም ሆነ እራሱን ቀይሮ ፍትሃዊ ስርዓት እስኪሆን ድረስ ትግሉ የሚቀጥል እንጂ የሚቃረጥም ሆነ የሚዳከም አይደለም።

እንደ አለመታደል ሆኖ በኢትዮጵያ ስልጣነ ወንበር ላይ የተፈናጠጠው ህወሃት መራሹ ስርዓት እንደ ሌሎች ሀገር ገዢዎች እራሱን የመለወጥ ተፈጥሮአዊ ጉድለት የተጸናወተው መሆኑ ከድርጅቱ በኩል ለውጥ ይከሰታል ብሎ ከመጠበቅ ድርጅቱን ከመሰረቱ ፈንቅሎ ለመጣል ትግሉን ያለማቃረጥ ማካሄድ እንዳለብን ማድረጉ ነው።

ጭቆናውና ጨቋኙ በስልጣን እስካለ -ሕዝባዊው ትግል በሕዝባዊው ዓመጽ ታጅቦ እስከድል ይቀጥላል።

ቸር እንሰንብት።

--------

ለጥያቄም ሆነ ለአስተያየት በኢትዮሚዲያ ኢሜይል ወይም teklu7@gmail.com
 ጻፉልኝ -እመልሳለሁ።